Refugee
Sponsorship
Training
Program

# በግል የሚደገፉ ስደተኞች መብቶች




ወደ Canada እንኳን በደህና መጡ! እርስዎ (Quebec ን ሳይጨምር) በ Canada ውስጥ የሚኖሩ በግል የሚደገፉ ስደተኛ ከሆኑ፣ ይህ የመረጃ ምንጭ ለእርስዎ ነው። Quebec ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ እባክዎ ለመረጃ *Immigration, Diversité et Inclusion* ያግኙ።

በግል የሚደገፍ ማለት Canada ውስጥ አንድ የሰዎች ስብስብ እርስዎን ወደ እዚህ ለማምጣት ማመልከቻ አስገብቷል፣ እና ለእርስዎ የድጋፍ ጊዜ በቁርጠኝነት እርስዎን ለመደገፍ እና የመሰረታዊ ወጪዎችዎን ለመሸፈን ወስኗል።

ይህ የመረጃ ምንጭ የእርስዎን **መብቶች**፣ እና **ከእርስዎ ደጋፊዎች ምን መጠበቅ እንዳለበዎት** ያብራራል። **ስለ ድጋፉ ካሳሰበዎት፣ ወይም የሚገባዎትን ድጋፍ እያገኙ እንዳልሆነ ካመኑ ምን ማድረግ እንዳለበዎት** ደግሞ ያብራራል።

## የግል ደጋፊዎች እነማን ናቸው?

የግል ደጋፊዎች እርስዎ ወደ Canada እንዲመጡ በጋራ የመጡ በጎ ፈቃደኞች ናቸው። ለእርስዎ የገንዘብ እና የግል ወጪ ድጋፍ ለመስጠት በቁርጠኝነት ወስነዋል። የእርስዎን ደጋፊዎች ሊያውቋቸው ይችላሉ፣ የእርስዎ የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ወይም የእርስዎ ደጋፊዎች እርስዎን ለመርዳት የሚፈልጉ ባይተዋር ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ እና በመጪዎቹ ወራት ውስጥ የሚያውቋቸው ናቸው።

## የእርስዎ የድጋፍ ጊዜ ርዝመት ምን ያህል ነው?

በአጠቃላይ፣ የድጋፍ ጊዜ **አንድ አመት** ነው። በጣም ባልተለመደ ሁኔታዎች፣ እርስዎ Canada ከመድረስዎ በፊት የካናዳ ፍልሰተኞች፣ ስደተኞች እና ዜግነት መምሪያ (IRCC) ደጋፊዎችን ከአንድ አመት በላይ ድጋፍ እንዲሰጡ ከጠየቀ፤ የድጋፍ ጊዜ ከአንድ አመት በላይ ሊረዝም ይችላል። የእርስዎ የድጋፍ ጊዜ ከአንድ አመት በላይ ከሆነ፣ ይህን በ IRCC እንዲያውቁት ተደርገው ይሆናል።

## ከደጋፊዎችዎ ምን ማግኘት አለብዎት?

**1) <u>የገንዘብ ድጋፍ</u> የእርስዎን መሰረታዊ ወጪዎች ለአንድ አመት የሚሸፍን፣ ወይም እርስዎ ራስዎን-መደገፍ እስከሚችሉ ድረስ፣ የትኛውም ቀድሞ የመጣ።**

ደጋፊዎ በ Canada ውስጥ ባሉበት የመጀመሪያ አመት ወቅት እርስዎን በገንዘብ የመደገፍ ወይም እርስዎ ራስዎን-መደገፍ እስከሚችሉ ድረስ፣ የትኛውም ቀድሞ የመጣ፣ ኃላፊነት አለበት። ድጋፉ በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ ሊያካት ይችላል፣ አልያም ደጋፊው እንደ ጠረጴዛ፣ወንበር፣ ሶፋ፣ የቤት ውስጥ እቃዎች፣ አልባሳት የመሰሉ ነገሮችን ደግሞ ሊሰጥዎ ይችላል።



© 2016 Refugee Sponsorship Training Program, Catholic Crosscultural Services

በቂ ገንዘብ ሊሰጥዎ ይገባል **ወይም** የተለገሱ ነገሮች ለእርስዎ የሚቀርብልዎት እንደ፡-

a) መኖሪያ (ክፍል፣ አፓርትማ ወይም የሚኖሩበት ቤት)
b) ምግብ
c) ልብስ
d) የአካባቢ መጓጓዣ (ለምሳሌ፣ የህዝብ አውቶቢሶች ወይም ባቡሮች)

በ Blended Visa Office-Referred (BVOR) መርሃ ግብር ስር የተደገፉ ከሆነ፣ Canada ውስጥ በሆኑ ሁለተኛ ወር ጀምሮ የ Canada መንግስት ለስድስት ወራት ያህል መሰረታዊ ወጪዎችዎን የሚሸፍን ወርሃዊ ቼክ ይሰጥዎታል። የእርስዎ ደጋፊ ቡድን ኃላፊነት አለበት ለ፡-

- ለእርስዎ ገንዘብ በመስጠት ወይም ቤትዎን የሚያደራጅ እቃዎች፣ እንደ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ሶፋ፣ የማድ ቤት አቅርቦቶች፣ የማጽጃ ምርቶች፣ ብርድ ልብስ፣ የአልጋ ልብስ፣ አንሶላ፣ ትራስ፣ ጥቂት ምግብ፣ ኪራይ እና ለመብራት፣ ውሃ፣ ጋዝ ተቀማጮች፣ አንዳንድ አልባሳት፣ ወዘተ የመሳሰሉ። ከእነዚህ ነገሮች አንዳንዶቹ የተለገሱ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ለእርስዎ በቂ ገንዘብ ወይም ወርሃዊ ወጪዎችዎን የሚሸፍን ነገሮች (ከላይ የተዘረዘሩትን) Canada ውስጥ በሆኑበት **የመጀመሪያ ወር** ላይ መስጠት።
- ለእርስዎ በቂ ገንዘብ ወይም ወርሃዊ ወጪዎችዎን የሚሸፍን ነገሮች (ከላይ የተዘረዘሩትን) Canada ውስጥ በሆኑበት የድጋፍ ጊዜዎ **የመጀመሪያ አምስት ወራት** ላይ፣ ወይም እርስዎ ራስዎን እና ቤተሰብዎን መደገፍ እስከሚችሉ ድረስ፣ የትኛውም ቀድሞ የመጣ መስጠት።

በ Canada የመጀመሪያ አመትዎ ውስጥ ስራ ካገኙ፣ ደጋፊዎችዎ ለእርስዎ የሚሰጡትን ገንዘብ መጠን ሊቀንሱ ይችላሉ። ሙሉ በሙሉ ራስዎን እና ቤተሰብዎን መደገፍ ከቻሉ፣ እርስዎን የሚደግፈው ቡድን ለእርስዎ የገንዘብ ድጋፍ እያደረገ መቀጠል አያስፈልገውም፤ ለእርስዎ ድጋፍ እየሰጡ መቀጠልም ሆነ አለመቀጠል ውሳኔ የእነርሱ ነው።ሆኖም ግን፣ በድጋፍ ጊዜ ስራዎን ካጡ፣ ደጋፊዎችዎ ለእርስዎ የገንዘብ ድጋፉን መስጠት እንደገና መጀመር አለባቸው። በመሰረቱ፣ **የደጋፊው ቡድን ከላይ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ነገሮች በመላው የድገፋ ጊዜ ሁሉንም የሚችሉ መሆንዎትን ማረጋገጥ አለባቸው።** መስራት ሲጀምሩ የደጋፊው ቡድን ምን ያህል ድጋፍ ሊሰጥዎ እንዳቀዱ ውይይቶችን ማድረግ መልካም ሃሳብ ነው።

እራስዎን እና ቤተሰብዎን ሙሉ በሙሉ ለመደገፍ የሚያስችል በቂ ገንዘብ አስቀድሞ ካለዎት የግል ደጋፊዎች ለእርስዎ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት አይጠበቅባቸውም። ወደ Canada ገንዘብ ይዘው ከመጡ፣ የእርስዎ ደጋፊ ቡድን ለኑሮ ወጪዎችዎ እንዲያዋጡ ሊጠይቁዎ ይችላሉ። በመጨረሻም ደጋፊዎችዎ ሁሉንም መሰረታዊ ፍላጎቶችዎን የሚሸፍን በቂ ገንዘብ እንዳለዎ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

እርስዎ የሚቀበሉት ቤት እና እቃዎች ጥራት የሚወሰነው ቡድኑ ለእርስዎ ማዋጣት በቻለው ገንዘብ ልክ ነው። ምንም እንኳ ለእርስዎ የተሰጡት እቃዎች እና የተሰናዳው መኖሪያ ቦታ ቅንጡ ላይሆን ይችላል፣ በቂ ግን መሆን አለባቸው። ቤትዎ ቤተሰብዎን ሁሉ ማኖር የሚችል መሆን አለበት፣ እናም እርስዎን እና ቤተሰብዎን በደንብ-መመገብ እና ጤናማ አድርጎ የሚጠብቅ በቂ ገንዘብ ሊኖርዎት ይገባል።

ሌሎች ስደተኞች ከእርስዎ የበለጠ ወይም ያነሰ ገንዘብ እና እቃዎች ተሰጥቷቸው ሊሆን ይችላል። ይህም ሊሆን የቻለበት አንዳንድ ደጋፊ ቡድኖች ለድጋፉ ከፍተኛ ገንዘብ ማዋጣት ስለቻሉ ነው፣ ሌሎች ደግሞ ማዋጣት የቻሉት የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ መጠን ገንዘብ ብቻ ነው። ሌሎች ደጋፊ ቡድኖች ደግሞ የበለጠ ገንዘብ እና ጥቂት የተለገሱ እቃዎች ሲሰጡ አንዳንድ ደጋፊ ቡድኖች



© 2016 Refugee Sponsorship Training Program, Catholic Crosscultural Services

ደግሞ ለእነርሱ ለሚደግፏቸው አዲስ መጤዎች ነጻ ኪራይ ወይም የተለገሱ እቃዎችን እንዲያገኑ ያዘጋጁ በመሆኑ ምክንያት ሊሆን ይችላል እና ስለዚህ በየወሩ ያነሰ ገንዘብ ይሰጧቸዋል። ሁሉም ቡድኖች የተለያዩ ናቸው። **በአነስተኛው፣ ደጋፊዎች በእርስዎ አካባቢ ውስጥ ካለ ማህበራዊ እገዛ መጠን ጋር እኩል የሆነ የድጋፍ ደረጃ እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል እና ሁሉንም መሰረታዊ ወጪዎችዎን የሚሸፍን በቂ ድጋፍ መስጠት አለባቸው።** በተጨማሪም የተለያዩ ፈርጆች የመጡ ስደተኞች (እንደ መንግስት ድጋፍ ያሉ) የተለያዩ አማራጮች እንዳሏቸው ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

## 2) በድጋፍ ወቅት ጊዜ የሚደረግ <u>የማቋቋሚያ ድጋፍ</u>።

የእርስዎ ደጋፊዎች በ Canada ውስጥ እንዲቋቋሙ እና እንዲላመዱ ሊያግዙዎት ይገባል። ይህ ብዙ ተግባራትን ያካትታል፣ የሚከተሉትን ያጠቃላል (ነገር ግን አይወሰንም)፦

- ***መኖሪያ ቤት***
  - ለእርስዎ መኖሪያ ቤት ፈልጎ ማግኘት፣ ወይም ቤት እንዲያገኙ መርዳት።

- ***የመተዋወቂያ ክፍለ ትምህርት***
  - እንደ አውቶቡሶች እና ባቡሮች የመሳሰሉ የህዝብ መጓጓዣን እንዴት እንደሚጠቀሙ ያስተምርዎታል
  - የእርስዎን ማህበረሰብ አዙሮ ማሳየት እና በቅርብ የሚገኙ የምግብ መደብሮችን እንዲያገኙ መርዳት
  - በ Canada ውስጥ ያሉ ህጎችን ማብራራት።

- ***የጤና እንክብካቤ***
  - ለክፍለ ግዛት የጤና ካርድዎ እና ለጊዜያዊ የፌደራል የጤና መርሃግብር (IFHP) እንዲያመለክቱ እርስዎን መርዳት
  - ሐኪም፣ ጥርስ ሐኪም እና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች ለእርስዎ ፈልጎ ማግኘት
  - የጤና አገልግሎቶችን ያብራራል።

- ***ትምህርት***
  - በእንግሊዝኛ ወይም በፈረንሳይኛ ክፍሎች እንዲመዘገቡ መርዳት
  - ልጆችዎን በትምህርት ቤት እንዲያስመዘግቡ መርዳት።

- ***አስፈላጊ ሰነዶች እና አገልግሎቶች***
  - የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ፣ ለማህበራዊ ዋስትና ቁጥር እንዲያመለክቱ፣ እና ልጆች ካልዎት፤ ለልጅ ታክስ ድጎማ እንዲያመለክቱ መርዳት።

- ***ትርጓሜ***
  - አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚ በማቅረብ።

- ***ሥራ***
  - ስራ አፈላላጊ አገልግሎቶች ጋር እርስዎን ማገናኘት።

- ***የመረጃ ምንጮች እና አገልግሎቶች***
  - ይህም እንደ አቋቋሚ ሠራተኛ፣ አግባብ ካላቸው የመረጃ ምንጮች እና አገልግሎቶች ጋር እርስዎን ማገናኘት።

*(በአካባቢዎ ውስጥ ስደተኛ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ፦ http://www.cic.gc.ca/english/newcomers/map/services.asp)*

በተጨማሪም በ Canada አዲሱን ኑሮዎን ሲላመዱ ደጋፊዎችዎ **ስሜታዊ እና ሞራላዊ ድጋፍ** ሊሰጥዎ ይገባል።



© 2016 Refugee Sponsorship Training Program, Catholic Crosscultural Services

## የእርስዎ የመቋቋም ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

አንዴ Canada ከደረሱ በኋላ በተቻለ ፍጥነት እራስዎን ለመቻል ማንኛውንም ጥረት እንደሚያደርጉ ይጠበቅብዎታል። ይህም እንግሊዘኛ ወይም ፈረንሳይኛ ክፍሎች ትምህርት መከታተል፣ በ Canada ሕይወት ውስጥ ኑሮዎን ለማረጋጋት ሊረዳዎ ከሚችለው ከመቋቋሚያ ጉዳይ ሠራተኛ ጋር መገናኘት እና የሚችሉ ከሆነ ሥራ መፈለግን ሊያካትት ይችላል።
ምንም እንኳን በ Canada ውስጥ በመጀመሪያ አመትዎ ራስዎን እና ቤተሰብዎን ሠርተው እንዲደግፉ ባይገደዱም፣ የድጋፍ ጊዜ ካለፈ በኋላ ራስዎን እና ቤተሰብዎን እንዴት አርገው ማገዝ እንደፈለጉ እቅድ ማዘጋጀት መልካም እንደሆነ ይመከራል።

### በ Canada ውስጥ ወደ አንድ የተለየ ከተማ ውስጥ ለመልቀቅ ቢመርጡ ምን ይከሰታል?

Canada ውስጥ ወደ ማንኛውም ቦታ እንዲዛወሩ ይፈቀድልዎታል። ይሁን እንጂ፣ እርስዎ በፈቃደኝነት ሌላ የ Canada ክፍል ለመሄድ ከመረጡ የእርስዎ ደጋፊዎች የገንዘብ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ለእርስዎ ለመስጠት አይችሉ ይሆናል። የመንግሥት ድጋፍ ለሚያገኙ አዲስ መጤዎች ለቀሪው የድጋፍ ጊዜ ከ IRCC ተጨማሪ የገንዘብ እገዛ ማግኘት ላይችሉ ይችላሉ።

የግል ደጋፊዎች እርስዎ በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ የሚኖሩ እንደሆኑ በመረዳት እርስዎን ለመደገፍ ቆርጠዋል። ምንም እንኳን በ Canada ውስጥ በማንኛውም ቦታ የመንቀሳቀስ መብት ቢኖርዎትም፣ የግል ደጋፊዎችዎ በማኅበረሰባቸው ውስጥ እያሉ ለመጀመሪያ ዓመትዎ ብቻ እርስዎን እንዲረዱዎት ይጠበቅባቸዋል። እርስዎ ከለቀቁ፣ ደጋፊዎችዎ በአዲሱ ማህበረሰብዎ ውስጥ አንድ ደጋፊ ቡድን ሊፈልጉልዎት ይገባል። ነገር ግን፣ ይህን ለማድረግ ካልቻሉ፣ ተጨማሪ የደጋፊ እገዛ ላያገኙ ይችላሉ።

### ደጋፊዎችዎ ማድረግ የማይፈቀድላቸው ምንድን ናቸው?

ድጋፊዎችዎ እዚህ ያሉት እርስዎን ለመደገፍ ነው። እነሱ አይፈቀዱም:-

- **እርስዎ** የእርስዎን ድጋፍ ለመክፈል፣ ማንኛውም ክፍያዎችን ጨምሮ ወይም በ Canada ውስጥ የኑሮ ወጪዎችን ለመክፈል ገንዘብ (እንመልስልዎታለን ቢልዎትም እንኳ) **ከመድረስዎ በፊት** ከእርስዎ ማንኛውም ገንዘብ መውሰድ
- ከደረሱ በኋላ እርስዎን በመደገፋቸው መልሰው እንዲከፍሏቸው ከእርስዎ ማንኛውም ገንዘብ መውሰድ (ለራስዎ ወጪዎች ለመክፈል ያመጡትን ገንዘብ እንዲጠቀሙ ሊጠይቁዎት እንደሚችሉ በማስታወስ)
- እንዲሰሩ ማስገደድ
- በነፃ ለእነርሱ እንዲሰሩ መጠየቅ
- ማድረግ የማያስደስትዎን ነገሮች ሁሉ እንዲፈጽሙ ማስገደድ።

ደጋፊዎች በ Canada ውስጥ ኑሮን ለመለማመድ እንዲረዳዎ በፈቃደኝነት ቆርጠው ወስነዋል፣ እና በምላሹ ምንም ሊጠብቁ ወይም ሊጠይቁ ኣይችሉም።



© UNHCR



© 2016 Refugee Sponsorship Training Program, Catholic Crosscultural Services

## ከደጋፊዎችዎ በቂ ድጋፍ እያገኙ ካልሆነ ምን ማድረግ ይጠበቅብዎታል?

የግል ደጋፊዎች ሊሰጡ የሚጠበቀውን ድጋፍ እየሰጡዎት እንዳልሆነ ካመኑና፣ ይህን ለማድረግ ካልከበደዎት፤ ስለ እሳቤዎችዎ ለደጋፊዎችዎ ያነጋግሩዋቸው። በድርጅቱ በኩል እርስዎን ከደገፉዎት (ለምሳሌ፣ የድጋፍ ስምምነት ባለቤት)፣ የሚያሳስብዎት ነገር ለድርጅቱ ያካፍሉ። አሁንም ድጋፍ የማይቀበሉ ከሆነ ወይም ደጋፊዎችዎን ለመቅረብ የሚፈሩ ከሆነ፣ **የፍልሰት ስደተኞች እና Canada ዜግነት (IRCC) ማነጋገር** አለብዎት። IRCC ን ማነጋገር ምንም ጉዳት አያስከትልም፣ እና የቋሚ ነዋሪነትዎ ሁኔታም አይጎዳውም። IRCC ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት ይሞክራል።

IRCC ን ማነጋገር ይችላሉ በ፡-

- ኢሜይል ለመላክ **IRCC.INPSR-PPPRRI.IRCC@cic.gc.ca** ወደ አግባብ ካለው የአካባቢው IRCC ቢሮ ለመገናኘት፣ ወይም
- IRCC አጠቃላይ የጥሪ ማእከል በ 1-888-242-2100 በመደወል።

በመጨረሻም፣ በአካባቢዎ የ IRCC ቢሮ (በአብዛኛውን ጊዜም በአካባቢዎ የሚገኝ የ IRCC ቢሮ ነው) ጋር ይገናኛሉ።

የአካባቢው የ IRCC ቢሮ ጉዳዩን በተመለከተ ጥያቄዎች ይጠይቅዎታል፣ እንዲሁም ከእርስዎ የድጋፍ ቡድን ጋር ይነጋገሩ ይሆናል። ምን ያህል የገንዘብ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ እንደሚሰጥዎ እና በቂ ድጋፍ የማያገኙበትን ምክንያቶች የመሳሰሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይሞክራሉ። ይህንን ጥናት እየሰሩ እያለ፣ የአካባቢው የ IRCC ቢሮ አስቸኳይ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግዎት ካረጋገጠ፣ አንዳንድ የአስቸኳይ ጊዜ ገንዘብ ሊሰጡዎት ይችሉ ይሆናል። የአካባቢው የ IRCC ቢሮ ለእርስዎ የፋይናንስ እና የማቋቋሚያ ድጋፍ ማን እንደሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይወስናሉ። በቂ ድጋፍ የማያገኙ መሆኑ እውነት ሆኖ ከተገኘ፣ እና የእርስዎ ደጋፊ ቡድን ለእርስዎ ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት ካልቻሉ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ “sponsorship breakdown” ሊያወጁ ይችላሉ። ይህ ማለት የእርስዎ ድጋፍ አድራጊ ቡድን ለቀሪው የድጋፍ ጊዜ ለእንደዚህ ያለ የገንዘብ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ለእርስዎ ለማቅረብ ሃላፊነት አይኖረውም ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- ሌላ ድጋፍ አድራጊ ቡድን ይሰጥዎታል፣ ወይም
- የመንግስት ገንዘብ ይሰጥዎታል፣ ወይም
- ለክልላዊ የማህበራዊ እርዳታን ማመልከት እንደሚችሉ ይነገርዎታል።

በጉዳዩ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ በድጋፍ አድራጊው ቡድን አንዳንድ እርምጃዎችን ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ፣ ለመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ ወይም እርስዎ የሚቀበሉትን ክልላዊ የማህበራዊ እርዳታን ለመንግስት እንዲከፍሉ ሊጠይቁ ይችላሉ።

መፍትሄዎችን እና የሚያስከትሉት እርምጃ የሚወሰነው በጉዳይ ጉዳይ መሰረት በማድረግ በ IRCC በኩል መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

## እንግልት፣ ብዝበዛ ወይም ማጎሳቆል ከደረሰብዎ ምን ማድረግ ይጠበቅብዎታል?

በድጋፍ አድራጊዎችዎ እንግልት እየተደረገብዎት ወይም እየተበዘበዙ እንደሆነ ካመኑ እባክዎ ወዲያውኑ IRCC በ IRCC.INPSR-PPPRRI.IRCC@cic.gc.ca.ያግኙ ብዙ ዓይነት የእንግልት እና ብዝበዛ ምሳሌዎች አሉ እነኚህን ጨምሮ፡-



© 2016 Refugee Sponsorship Training Program, Catholic Crosscultural Services

- ማስፈራራት፤
- ለደጋፊዎች ገንዘብ ለመስጠት መገደድ፤
- ቤቱን ለቀው እንዲወጡ አለመፈቀድ፤
- እንዲሰሩ መገደድ፤
- ለማድረግ የማይመችዎትን ነገሮች እንዲያደርጉ መገደድ፤

ለማንኛውም ከባድ ወይም አጣዳፊ ጉዳዮች ፖሊስን ያነጋግሩ። ድንገተኛ ከሆነ፣ አስቸኳይ እርዳታ ለማግኘት 911 ይደውሉ። አስቸኳይ ጉዳዮችን የሚያካቱት (ግን በእነዚህ አይወሰንም)፡-

- አንድ ሰው ለእርስዎ ወይም ለቤተሰብዎ ሁከት እየፈጠረ ከሆነ፤
- አንድ ሰው ለእርስዎ ወይም ለቤተሰብዎ ሁከት እንደሚፈጥር ከስጉ፤
- ማንኛውም ማጎሳቆል፣ አካላዊ ወይም ወሲባዊ በደልንም ጨምሮ ካጋጠመዎ።

## ያለዎትን አሳሳቢ ሁኔታዎች ለ IRCC ካሳወቁ ምን ይደርስብዎታል?

ከእርስዎ ደጋፊዎች በቂ የገንዘብ ወይም የመቋቋሚያ ድጋፍ እያገኙ ካልሆነ፣ ወይም እርስዎ እንግልት፣ ብዘበዛ ወይም መጎሳቆል ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፡ ጨምሮ ስለ መደገፍ ስጋቶች ካለዎት IRCC ን እርዳት ቢጠይቁ ምንም አያስከትልብዎትም።

ስጋትዎን ለ (IRCC) ሪፖርት ካደረጉ፤ Canada ውስጥ የቋሚ የመኖሪያ ፈቃድዎን የማጣት **ስጋት የለውም**። የእርስዎ ሁኔታ በተመሳሳይ ይቆያል፣ እና IRCC ለገጠመዎት ችግር መፍትሔ ለማግኘት ይሞክራል።

## የእርስዎ መብቶች ምንድን ናቸው?

ከእርስዎ ድጋፍ አድራጊ ቡድን ጋር ያልዎትን ማንኛውንም የሚያሳስብዎትን ነገር የመግለጽ መብት አለዎት። ለምሳሌ፣ ያለ እርስዎ ስምምነት መረጃን ወይም የእርስዎን ምስል ደጋፊዎች ሲያሳትሙ፣ ወይም በእርስዎ ምትክ ውሳኔዎች ሲያደርጉ፣ ለደጋፊችዎ የሚያሳስብዎትን ነገር የማንሳት መብት አለዎት።

በተጨማሪም ከግል ድጋፍ ሰጪዎች ከዚህ በላይ የተብራሩትን የገንዘብ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ የማግኘት መብት አለዎት።

ያልዎትን የሚያሳስብዎትን ነገር IRCC አግኝተው የማንሳት፣ እና አስፈላጊ ከሆነ ፖሊስን ማነጋገር መብትዎ ነው።

## የበለጠ መረጃ የት ማግኘት ይችላሉ?

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የስደተኛ ድጋፍ

ስልጠና መርሃ ግብር RSTP)
ያግኙ፡- **ስልክ፡- 1-877-290-1701**
**ኢሜይል፡- info@rstp.ca**

© 2016 Refugee Sponsorship Training Program, Catholic Crosscultural Services